# የአሲምባ ውይይት መድረክ ፕሮግራም

ቅዳሜ የካቲት 21 ቀን 2007 ዓ.ም.
(February 28, 2015)

የአሲምባ ውይይት መድረክ የፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ ጣቢያን ለማጠናከር (በሳተላይት ደረጃ እንዲተላለፍ) ለማድረግ በሚደረገው ርብርቦሽ ተሳታፊ በመሆን እነሆ የፊታችን ቅዳሜ ልዩ ዝግጅት ይዞ ቀርቧል። በዓለም ዙሪያ ያላችሁ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ይህንን በኢትዮጵያውያን፣ ለኢትዮጵያውያን፣ ስለኢትዮጵያውያን የአንድነት ድምጽ ሆኖ ያገለገለንን ራዲዮ ጣቢያ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ አማራጭ ለማጠናከር በምናደረገው ዝግጅት ተሳታፊ እንድትሆኑ በማክበር እንጠራለን።

በዚህ ቀን የራዲዮ ጣቢያው ዝግጅት ክፍል አባላት፣ ከኢሕአፓ የአመራር አባላት ዶ/ር ዘነበና አቶ ፋሲካ በለጠ ፣ የኢትዮጵያ ፓለቲካ እሥረኞች አንድነት ኮሚቴ መሪ አቶ አሊ ሁሴንና ሌሎችም በመገኘት ስለ ራዲዮ ጣቢያው አጀማመርና እስካሁን ስላደረጋቸው አገልግሎቶች ሰፋ ያለ ማብራሪያና ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ይዘውልን ይቀርባሉ።

ወገኖቻችንም በዚሁ ዕለት በአሲምባ የፓልቶክ የውይይት በድረክ በመገኘት ይህንን የኢትዮጵያውያን የትግል ራዲዮ ጣቢያ ለማጠናከር በምናደርገው ጥረት ተሳታፊ እንድትሆኑ እንጋብዛለን።

የአሲምባ ውይይት መድረክ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ስለ ሀገራችን ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ የሰከነ ውይይት የሚያደርጉበት፣ የተለያዩ ሀሳቦች የሚንሸራሸሩበት ነጻ የውይይት መድረክ ነው።

የአሲምባ ውይይት መድረክ ከቀኑ ሁለት ሰዓት አንደ ዋሺንግተን ዲሲ ሰዓት አቆጣጠር ጀምሮ ይከፈታል።

የአሲምባ ውይይት መድረክ